# **የኢትዮጵያ ሕዝብ፣ አገር-ወዳድና ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች እና ኢሕአዴግ፤ ከዚኽ ወዴት?**

*ከአያል ሰው ደሴ፤- የግል አስተያየት*

***ክፍል አሥራ-አንድ** (ከክፍል አሥር የቀጠለ)፤-...*

*ሐ) አመራር፤-* ቀደም-ሲል እንዳየነውና ወደ-ፊትም እንደምንመለከተው ለማንኛውም የተናጠልም ሆነ የጋራ ትግል መሣካት ወይም ውድቀት አመራር ቁልፍ የሆነ ሚና አለው:: በመሠረቱ የትግል ድርጅት አመራር ሰጭ መሆን ከፍተኛ ኃላፊነት ስለሆነ በኀሊና ተገዥነት አገልግሎት የሚሰጥበት እንጂ የግል ጥቅም የሚገኝበትም ሆነ አጉል ዝና የሚፈለግበት ሹመት ተደርጎ መታዬት አይኖርበትም:: (በዚኽ ርዕሰ-ጉዳይ ላይ በመጨረሻው ክፍል ትንሽ ዘርዘር ተደርጎ ቀርቧል::) የአማራጭ ኃይሎች ምክር-ቤት በተመሠረተበት መንፈስ ለተጠበቀው ውጤት እንዳይበቃ ካደረጉት ዋና ዋና ምክንያቶች ውስጥም አንዱ የአመራር ችግር መሆኑ ግልጥ ነው:: ይኽ ደግሞ ሁለት ገፅታዎች አሉት:: አንደኛው <u>አለመተማመን</u> የፈጠረው ችግር ሲሆን ሁለተኛው እራሱ ኃላፊነት የተሰጠው ክፍል ድክመት ይሆናል:: ሁለተኛው ክፍል በተራው የራሱ ሁለት ዘርፎች አሉት:: እነሱም ራሱ ምክር-ቤቱን እንዲመሩ ኃላፊነት በተጣለባቸው ወገኖች በኩል የተከሰተ የግልና የወል-ኃላፊነትን መወጣት አለመቻል እና ለመጀመሪያው ድክመት አስተዋፅዖ አድራጊ ሆኖ የምናገኘው የአባል ድርጅቶች አመራ ክፍሎችን የሚመለከት ይሆናል::

የኢሰዴአኃ አመራርን በተመለከተ ከገጠሙት ችግሮች ውስጥ አለመተማመን አንዱና ዋነኛው ምክንያት ሲሆን፣ ይኽ ደግሞ ከሌላ ሣይሆን ኢሰዴአኃ ካሰባሰባቸውና በአባልነት ካቀፋቸው ድርጅቶች የፖለቲካ ፍልሥፍናና የአደረጃጀት ባኅሪ የመነጨ ነው:: የምክር-ቤቱ አባል ድርጅቶች በልዩ ልዩ የፖለቲካ እምነት ሥር እና ለተለያዩ ግቦች የቆሙ አካሎች እንደነበሩ ይታወቃል:: እነዚኽን በማስተባበር በአንድ አካልነት እንዲመሩ ኃላፊነት የሚሰጣቸው ወገኖች ደግሞ ከዚሁ ስብጥር ውስጥ የተመረጡ መሆናቸው የግድ ነው:: እያንዳንዱ የኢሰዴአኃ ምክር-ቤት አባል ድርጅት ከሌሎቹ የተለየ ድርጅት ሆኖ እንዲቆም ያደረጉት የራሱ የሆኑ እምነቶችና ባኅሪያት ስላሉት፤ ከነዚኽ መኻል ለመሪነት በተመረጡትና በቀረው ክፍል በኩል የሚኖረውን ግንኙነት፣ አመኔታ የማሳደርና የመቀበል ጉዳይን የሚወስነው መደበኛ በሆነ ዴሞክራሲያዊ የአብላጫ ድምፅ ከመመረጥ ጋርም ሆነ የግድ ከተመረጡት ግለሰቦች ማንነት ጋር የተያያዘ ሣይሆን በዚያ እያንዳንዱ የድርጅት ተወካይ እምነቴ ብሎ በያዘው በጣም መሠረታዊ በሆነ የፖለቲካ ፍልሥፍና እና የፖለቲካ አቋም ላይ ያጠነጠነና በሱም ዙሪያ የሚሽከረከር ሆኖ እናገኘዋለን::

እንደ ኢሰዴአኃ ያለ ስብስብ ደግሞ ተራ ማኅበር ሣይሆን መሠረታዊ የሆኑ የፖለቲካ አመለካከቶችና እምነቶች ላይ የተመሠረተና ስብስቡም የፖለቲካ ጉዳይን የሚመለከትና ለዚያም የቆመ በመሆኑ አካሄዶች፣ አዝማሚያዎች፣ ግንኙነቶች፣ ትሥሥሮችና ስሊቶች ሁሉ እያንዳንዱ 'መርኄ' እና 'መተክሌ' ብሎ በያዘው ዙሪያ የሚውጠነጠኑና የሚመዘኑ በመሆኑ፣ ድርጅቶቹን የሚመሩት ሰዎችም የየድርጅታቸውን እምነት ስለሚያንፀባርቁና ቅድሚያም ለዚያ ስለሚሰጡ ሁሉንም የጋራ ትግሉን መሥመር ጠብቆ ለማስኬድና ለማስቀጠል ቀላል አይሆንም:: ያም በመሆኑ ነው ምንም እንኳ “የጋራ” በሚባሉ ስምምነት የተደረሰባቸው ዐብይ ጉዳዮች ላይ አብሮ ለመሥራት ውሳኔ ቢደረግም እንደ ኢሰዴአኃ ዓይነት ስብጥሩ የወጣ ኃይልን ማሰባሰብና በአንድ መሥመር ማስኬድ፣ አልፎም ዎጥ-አመራር ለመስጠት ከባድ የሚሆነው:: ስብስቡን እንዲመሩ ኃላፊነት የሚሰጣቸው ወገኖችም የሚገጥማቸው ችግር በአብዛኛው ከዚኹ የሚመነጭ ይሆናል:: ያ ችግር ግን አንድ-ጎንዮሽ ሣይሆን ወደ-ጎንም፣ ወደ-ላይና ወደ-ታችም ያየ ዙሪያ ጥምጥም ነው:: በምክር-ቤቱ ተፈጥሮ ባኅሪና በመሪው የፖለቲካ እምነት ዙሪያ የሚሽከረከር ተቃርኖ ላይ ያጠነጠነ ችግርም አባላት በአመራሩ፣ አንዱ በሌላው አባል ድርጅት ላይ ሙሉ መተማመን እንዳይኖር ያደርጋል:: ይኽም ሁሉም አባላት በአንድ መሥመር እንዲጓዙና በጋራ የተነደፈውን ትልም የተከተለ

አመርቂና ወሳኝ ትግል ለማድረግ ሥነ-ሥርዓትን የጠበቀና ወለም-ዘለም የሌለበት አመራርን ለመስጠት ስለማያስችል ጥረቱ ከጅምሩ እክል እንደሚገጥመውና ለውድቀቱም አስተዋፅዖ እንደሚኖረው ግልጥ ነው።

ይኸ ደግሞ በተለያዩ ጊዜዎች ለማሳሰብ እንደሞከርኩት በተለይ የፖለቲካ-ጎሠኝነት ከሚያስከትላቸው ጠንቆች አንደኛው እክል ነው። በዚኸ ፖለቲካ ውስጥ የተከተሩ ወገኖች ፍላጎት፣ ብቃትና ችሎታ ቢኖራቸውም ቅሉ እራሣቸውን አንዴ በተወሰነ አጥር ውስጥ እንዲገደቡ በማድረጋቸው እነሱ "የኔ" ነው ብለው ከሚቆጥሩት "ውጭ" ያለው ዜጋ እንደ "ባዕድ" እንደተርቆጠረ ስለሚያይ ሙሉ እምነቱን ጥሎ ሊከተላቸው እንደሚቸገር የታወቀ ነው። ስለሆነም ለዚኸና በዚኸ መርዘኛና ጠንቀኛ የፖለቲካ ጎሠኝነት/ጎጠኝነት ቅኝት ላይ ለተመሠረተ የፖለቲካ ፍልሥፍና የቆሙ ወገኖች አጠቃላይ ስብስቡን በኃላፊነት እንዲመሩ ዕድሉ ቢሰጣቸውም (በአጋጣሚም ይሁን በችሎታቸው) አስቀድመው ከዚያ ከ"ሌሎቹ" ከሚለያቸው መሠረታዊ እምነት/ፍልሥፍና በወጣ መልክ (እንዲያውም በተወሰኑት መኻል ለምሣሌ በማያጠያይቅ አገራዊ አንድነትና የመገንጠልም መብት አለኝ ብሎ በሚያምን አመለካከቶች ዓይነት አንዱ ለሌላው አቋምና እምነት ጨርሶ ተቃራኒ በሆነ ደረጃ ላይ ባሉበት ሁኔታ)፣ ስለ-አጠቃላዩ ማሰብና ማየት እንደሚችሉ በተጨባጭ የሚያረጋግጥ ነገር ስለ-ሌለ፣ መኖርም ስለማይችል አንዱ የሌላውን አቋም እንደ-እራሱ አድርጎ የመቀበልና ተፈላጊ የሆነውን አንዱ በሌላው ላይ አመኔታውን የመጣልና እርስ-በርስ የመተማመን ሁኔታን ለማግኘት በእጅጉ ይቸግራል። እንደሚታወቀው ማንም ሰው የፖለቲካ ፍልሥፍናውና እምነቱ ለአንድ ጎሣ/ብሔረሰብ ብቻ ሲሆንና አደረጃጀቱም ያንን መልክ ሲይዝ፣ ያ በራሱ ግለ-ሰቡ ስለ-"ቀረው" እኩል ትኩረት እንዳይኖረውም ሆነ መቆርቆር እንዳይችል ግርዶሽ ይሆንበታል። "ሌላውም" ያ ሰው የምር ጉዳይ ሲነሣ ለኔም እኩል ያስብልኛል፣ ይቆምልኛል የሚል ሙሉ እምነት እንዳይኖረው ቢያንስ ጥርጣሬ እንዲኖረው ያደርጋል። ሁሉም በየበኩሉ የሚያስበው፣ በዚያ "እኛ እና እነሱ" አፈረጃጀትን የግድ በሚል የፖለቲካ አደረጃጀት የተሠለፈ ክፍል "ብሶቴን እንደኔ ሆኖ አያይልኝም፣ እሱ የቆመው ለራሱ ክፍል ብቻ ነው" በሚል አሳዛዝኝ ስሊት ይሆናል። ያም በመሆኑ በጋራውና እያንዳንዱ በተናጠል በቆመበት መተክል ዙሪያ የተሰመሩ የልዩነት መሥመሮችን ተከትሎ ጎን-ለጎን የሆነ የጅብ ጉዞ እንዲጓዝ ያደርጋል። የዚያ ዓይነት ስሜት ደግሞ አንድ-ጎንዮሽ ሣይሆን በሁሉም በኩል የየራሱን ትርጉም የያዘና ከሁሉም በኩል በሁሉም ላይ ያጠላ አመለካከት ነው። ይኸ የተድበሰበሰ አካሄድም በኢሰዴአኃም ሆነ እስካሁን በተሞከሩ የጋራ ትግል መድረኮች ላይ በቀጣይነት የተንፀባረቀ በመሆኑ በግልጥ ማየቱ ተገቢ ይመስለኛል።

እንደሚታወቀው ይኸንን አገር-አቀፍና ኅብረ-ብሔራዊ ድርጅት በበላይ ኃላፊነት እንዲመሩ በዴሞክራሲያዊ መንገድ የተመረጡት ግለ-ሰብ (ዶ/ር በዬነ) የነበሩበት የፖለቲካ ድርጅት የወል መብትን የማስከበር እንጂ የመገንጠል ጥያቄን ያላነሣ ድርጅት መሆኑ ግልጥ ነው። ሆኖም በጎሣዊ የፖለቲካ ቅኝት ሥር ያለ በመሆኑና ኃላፊነቱ የተሰጣቸው ግለ-ሰብም በግለሰብ ደረጃ እንደ አገሪቱ ዜጋ በኢትዮጵያዊ አቋማቸው ላይ ጥያቄ ያልተነሣባቸው ቢሆንም፣ በወቅቱ የፖለቲካ-ጎሠኝነት መርኅ ላይ የቆመ ድርጅት መሪ በመሆናቸው በቀረው፣ በተለይም የፖለቲካ-ጎሠኝነትና ጎጠኝነት ፍልሥፍናን በማይቀበሉ ኅብረ-ብሔራዊ ድርጅቶችና ስብስቦች ዘንድ ሙሉ አመኔታቸውን ለመጣል እንደተቸገሩ ይታወቃል። ይኸ ደግሞ በታሪክ አጋጣሚ ግለ-ሰቡ ዶ/ር በዬነ ስለሆኑ ሣይሆን በወቅቱ የቆሙበት የፖለቲካ ፍልሥፍና እንደሆነ ከዚያም በኋላ በተደጋጋሚ የገጠመ ችግር እንደሆነ አይዘነጋም። ያ በአባል ድርጅቶች መኻል የነበረ አለመተማመን ኢሰዴአኃ በተቋቋመበት መንፈስ እንዳይንቀሣቀስ ቀስፎ እንደያዘውና ተልዕኮውን እንዳያሟላ እንቅፋት እንደሆነበት የታወቀ ነው። ይኸ የአመኔታ ጉድለት በምክር-ቤቱ ብቻ የተከሰተ ወይም በታሪክ አጋጣሚ በወቅቱ የስብስቡ መሪ ዶ/ር በዬነ (በዚያን ጊዜ የሐዲያ ብሔር ድርጅት ሊቀ-መንበር) ስለሆኑ ሣይሆን እስካሁን የሕወሓት አመራር ቢጥር-ቢግር ሊወጣው ያልቻለና የማይችል ችግር፣ ብዙ ታጋዮችን የተጠናወተና ማንም በፖለቲካ ጎሠኝነት/ጎጠኝነት ፍልሥፍና የቆመና በአገር-አቀፍ እንቅስቃሴ ቀጥተኛ ተሣትፎ ማድረግ የሚከጅል ሁሉ ደግሞ-ደጋግሞ ሊያጤነው የሚገባ ጉዳይ ነው። በዚኸ ረገድ በዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳ የዛሬ ዓመት ግድም የተወሰደው ደፋርና ከእምነት የመነጨ መሠረታዊ የአቋም ለውጥ በአብነት የሚዘከር ነው።

በግልባጩ በወቅቱ በነበረው የተበከለ የፖለቲካ-ጎሠኝነት ሁኔታ የኢሰዴአኃን አመራር በዋናነት የያዙት ከሕብረ-ብሔራዊ ድርጅቶች መሪዎች ውስጥ ቢሆን ኖሮም በሌሎቹ (ጎሣ/ብሔረሰብ) ድርጅቶች ዘንድ ደረጃው ሊለያይ ቢችልም ሙሉ አመኔታን የማግኘቱ ጉዳይ እርግጠኛ ያለመሆን ዕድሉ ነበር። ችግሩ አጠቃላይ ነባራዊ-ሁኔታ-ወለድ ነው የምለውም ለዚኽ ነው። ስለሆነም በተከሰተው የአለመተማመን ችግር ምክንያት የኢሰዴአኃ አመራር በአባል ድርጅቶች ዘንድ የሚጠበቀውን ሙሉ እምነት ላይ የተመሠረተ ትብብር የማግኘትም ሆነ አመራሩም በቀሩት አባላት ዘንድ ገላ-የሰደደ አመኔታ ያለው ትሥሥር እንዳይኖር አድርጓል። በዚኽ መሠረታዊ ችግር ምክንያትም ምክር-ቤቱ የተቃዋሚው ክፍል ተወካይ ሆኖ እንዳይገኝ አድርጎታል። ለምሣሌ በአሜሪካ ምክር-ቤት (ኮንግረስ) የአፍሪቃ ጉዳይ ንዑስ-ኮሚቴ የወቅቱ ሰብሳቢ በነበሩት በተከበሩ አቶ ሃሪ ጆንስተን የኢሕአዴግን የሽግግር-መንግሥትና ተቃዋሚውን ለማነጋገር በተዘጋጀው ስብሰባ ላይ ተቃዋሚው ክፍል በኢሰዴአኃ ምክር-ቤት ብቻ እንዲወከል በተለይ በሰሜን-አሜሪካው የምክር-ቤቱ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት የተደረገው ከፍተኛ መረባረብ ሳይሣካ የቀረው በራሱ በምክር-ቤቱ አመራር እና በቀሩት የተቃዋሚ ክፍል ድርጅቶች ቀና-ፍላጎትና ቁርጠኝነት ባለመገኘቱ ነው።(*1) ምንም እንኳ ቀደም-ሲል ምክር-ቤቱ ከጅምሩ በገጠሙት ብዙ እክሎች ምክንያት ነጥሮ-በወጣና በማያሻማ መልኩ የተቃዋሚው ጎራ ወኪል የመሆን አቅሙ የተዳከመና በተለይም ከአገር-ውጭ ከሚገኙ ድርጅቶች ጋር የነበረው ግንኙነት የለሰለሰና ሙሉ መተማመን የነበረበት ነው ማለት ባይቻልም፣ ያንን አጋጣሚ በአግባቡና በድፍረት መጠቀም ባለመቻሉ ኢሰዴአኃ እርባና፣ ተኣማኒነትና ተቀባይነት ያለው የተቃዋሚው ድምፅ እንዳይሆን አድርጎታል የሚል እምነት አለኝ። ብዙ ድርጅቶች ያንን የተቃዋሚው ክፍል ብቸኛ ተወካይና ተጠሪ የማድረግ ኃላፊነትን ለኢሰዴአኃ አሣልፎ ለመስጠት አለመፈለግ ብቻ ሣይሆን ጨርሶ ተቃዋሚ ሆነው መቅረባቸው ለኢሰዴአኃ መዳከምና እርባና ያለው የተቃዋሚው አለኝታ እንዳይሆን አድርጎታል። ኃላፊነት በተሰጣቸው ወገኖች ድክመትና በተቃዋሚው ክፍል በነበሩ ድርጅቶች ተቃውሞ መደጋገፍም ምክር-ቤቱ ሽባ እንዲሆን፣ የጋራ ጥረቱም መና እንዲቀር ሆኗል። (በሌላ ጊዜ በሠፊው ሊታይ የሚገባው ጉዳይ ነው።)

ምክር-ቤቱ ሲመሠረት ድርጅቱን እንዲመሩ ከተመረጡትና ኃላፊነት ከተሰጣቸው ውስጥ ከሊቀ-መንበሩ (ከዶክተር በዬነ ጴጥሮስ) በስተቀር ሌሎቹ ብዙም ሣይቆዩ በየተራ ተንጠባጥበው እንደተውት ይታወቃል። ይኽ እርምጃ ምክር-ቤቱ ላይ ሊኖር የሚችለው ተኣማኒነትና ተቀባይነት እንዲቀንስ ያደረገና ያም በመሆኑ ሕዝባዊ ድጋፍን በስፋት እንዳያገኝና ተልዕኮውንም በብቃት እንዳይወጣ አስተዋፅዖ አድርጓል የሚል እምነት አለኝ። በተመረጠው አመራር ውስጥ ተፈላጊው ቅርርብና አንድነት ባለመኖሩ፣ የአባል ድርጅቶች ተሣትፎ እንዲቀንስና የምክር-ቤቱ መሠረት እንዲጠብ፣ ተደማጭነቱም እንዲኮሰምን አስተዋፅዖ አድርጓል። ያም በመሆኑ ጅምሩ ላይ ኢሕአዴግ በምክር-ቤቱ እንቅስቃሴ ላይ የነበረው ሥጋት በኖ እንዲጠፋ ሆኗል። በሂደትም ከምክር-ቤቱ የሚቀርቡለትን የድርድር ጥሪዎችና ማሳሰቢያዎች ከመ-ጤፍ አልቆጠራቸውም፤ ቁም-ነገር ብሎም ለማስተናገድ አልተጨነቀባቸውም። በኢሰዴአኃ መሥራች ጉባዔ ላይ ኃላፊነት የተሰጣቸው የአመራር አባላት ሥርዓትን ጠብቀውና ለተጣለባቸው አደራ ተገቢውን ትኩረትና ቅድሚያ ሰጥተው ባለመሥራታቸውም አመራሩን ሊቀ-መንበር ሆነው የተመረጡት ሰው እጅ ተከማችቶ እንዲቀጥል አስችሏል። ኢሰዴአኃ ሲቋቋም የጋራ ትግሉን እንዲመሩ ከሊቀ-መንበሩ ጋር በምርጫ ኃላፊነት የተጣለባቸው ወገኖች የተሰጣቸውን ኃላፊነት በተውበት ጊዜ ያንን እርምጃ እንዲወስዱ ያደረጓቸው የየራሣቸው ምክንያቶች እንዳሏቸው አሌ አይባልም። ይሁንናም በተራ ሹመት ሣይሆን በሥነ-ሥርዓት ድምፅ ተሰጥቶ የተጣለባቸውን ኃላፊነት ጠቅላላ ጉባዔ ወይም አስፈላጊው አካል ተጠርቶ ችግሩን በማስረዳት ኃላፊነቱን ለሰጣቸው ክፍል መልሰው ማስረከብ ድፍረቱና አስተዋይነቱ ሊኖራቸው በተገባ ነበር። ያንን በማድረግ በምክር-ቤቱ አመራርና አያያዝ ዙሪያ ገና ከጠዋቱ የተከሰቱ አንዳንድ ችግሮችን ለማረምና ለማስተካከልም ዕድል ሊሰጥ፣ ትምሕርታዊም ሊሆን በቻለ ነበር። የተባለውን ስብሰባ ለመጥራት የሊቀ-መንበር ኃላፊነት በተሰጠው ሰው (እዚኽ ላይ ዶ/ር በዬነ) ፍላጎት አልነበረም የሚል ምክንያት ከነዚኽ ወገኖች በኩል ሊቀርብ ይችል ይሆናል። ሆኖም ኃላፊነት መልቀቁን መተዳደሪያ ደንቡን ተከትሎ በሥርዓት ማድረጉ በተገባ ነበር። እዚኽ

ላይ ቁም-ነገሩ የኃላፊነት፣ ያውም የሕዝብን ትግል ለመምራት በድምፅ የተሰጠን ኃላፊነት ከባድነትና ማንኛውም ድርጅት እመራበታለሁ (እተዳደርበታለሁ) ብሎ ላወጣው ደንብ ተገዥ መሆን እስካልቻለና ሥርዓት ከተጣሰ ድርጅቱ ለሕግ የበላይነትም ሆነ ለዴሞክራሲያዊ ሥርዓት መታገል የሚያዳግተው፣ አልፎም ብላሽ እንደሚሆን ሊታወቅ እንደሚገባ ለማሣሰብ ነው:: ማንኛውም በጉባዔ የተሰጠ ኃላፊነት በድርጅቱ ውስጥ በሚከሰት አለመግባባትም ይሁን በሌላ ምክንያት በቃል ወይም በተራ ደብዳቤ በማሳወቅ ብድግ ብሎ እንዲሁ የሚተው ሣይሆን፣ ኃላፊነቱን ኃላፊነት ለሰጠው ክፍል በሥርዓት መልሶ ማስረከብ ተገቢ ይሆናል:: በምክር-ቤቱ ኃላፊዎች በኩል ያ ሲሆን አልታየም:: እንዲያውም በአንዳንድ ድርጅቶች ውስጥ በጉባዔ ኃላፊነት የተሠጣቸው ወገኖች የተሰጣቸውን ኃላፊነት በሥርዓት ሣይሆን እንዲሁ በዘፈቀደ ሲተውት አንዳንዴም ያን መደበኛና ሕጋዊ አካሄድ ባለፈ አንድም እኔ ነኝ መሪ በሚል ጨርሶ የኃላፊነት ስሜት በጎደለው መልክ የነሱ ያልሆነ ኃላፊነትን ሙጥኝ የማለትና አጉል ፉክክር ውስጥ በመግባት፣ አለያም ተሽቀዳድሞ ሌላውን ተጠያቂ ለማድረግ በሚደረግ እኩይ ሙከራ በአደባባይ የሚደረግ መኳነንና መፏተግ አልፎ-አልፎ መከሰቱ፣ ለሕዝብ ከበሬታ የሌለው ድርጊትና ለተጠያቂነት ጨርሶ ዝግጁ አለመሆንን የሚያሣይ፣ ለኃላፊነትና ለዴሞክራሲ መርኅ ያለን አመለካከት የተዛባ መሆኑን የሚያስረዳ መቀጨት ያለበት ብልሹ ልማድ ይመስለኛል::

ይኸ ዙሪያ ጥምዝ የአመራር ችግር ኢሰዴአኃ የቆመለትን አገር-አቀፍ ትግል በአግባቡ ታግሎ ለውጤት እንዳይበቃ ተፈላጊ የሆነው መተማመን ላይ የተመሠረተ የአባላትን አንድነትና ሙሉ ድጋፍ ሊያገኝ አላስቻለውም:: የአባላትን አመኔታ በሚታይ መልክ ላላገኘና ሙሉ ትብብራቸውን ላጣ፣ ውስጣዊ ድርጅታዊ ጥንካሬ ለጎደለው ድርጅት ደግሞ ሕዝብ አመኔታውን፣ ከበሬታውንና ትብብሩን ሊለግሠው ይቸገራል:: የሕዝብ አመኔታና ሙሉ ድጋፍ የተነፈገው ድርጅት ደግሞ የተለመውን መሥመርና የቆመበትን መርኅ በተከተለ መልክ የትግሉን አካሄድና አመራር ቅድሚያ ከእጁ ሣይለቅ በመስክ ያለውን ሚዛን ለመቀየር እና የተፃራሪውን ክፍል ጆሮ የሳበም ሆነ አስገድዶ ትርጉም ወደ-አለው ድርድር ሊያመጣ የሚችል ትግል ማድረግ ይሣነዋል:: የኢትዮጵያ የሰላምና የዴሞክራሲ አማራጭ ኃይሎች ምክር-ቤትም ተስፋ የተጣለበትና ብዙ የተደከመበት ቢሆንም በተጠናወቱት የአደረጃጀትና የአወቃቀር፣ የጠራ የትግል-ትልም ጉድለትና ወሳኝ፣ ተአማኒነትና ሙሉ ተቀባይነት ያለው አመራር እጦት ምክንያት በተጠቀሱት አንገዋላይ አጣብቂኝ መኻል ሆኖ በስም ብቻ የቀረ ድርጅት ለመሆን በቅቷል::

*(*1) በጊዜው የኢሰዴአኃ ምክር-ቤት የሰሜን አሜሪካ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ምክር-ቤቱ የተቃዋሚው ጠንካራና ብቸኛ ድምፅ እንዲሆን ለአቶ ሃሪ ጆንስተን፣ ለክሊንተን አስተዳደር፣ ለልዩ ልዩ የኢትዮጵያ ጉዳይ የሚመለከታቸውና በአገራችን የዴሞክራሲ ግንባታውን ትግል ያግዛሉ ለተባሉት ሁሉ የቻለውን በአካል እያገኘ ለቀሩት ሰነዶችን እያዘጋጀ በመስጠት ያላሰለሰ ጥረት አድርጓል:: በቅርንጫፉ የውጭ-ጉዳይ ኮሚቴ ሰብሳቢ ዶ/ር ፀሐይ ብርሃነ-ሥላሴ አማካይነት ደብልዩ ፒ አፍ ደብልዩ በተሰኘው ራዲዮ የአንድ ሰዓት ፕሮግራም በመያዝ ስለ ምክር ቤቱ ገለፃ በማድረግ ጭምር አጠቃላይ ዘመቻ ተደርጓል:: በተጨማሪም በውጭ የሚገኙ የምክር-ቤቱ አባል ድርጅቶች አሰዴአኃን እንደ ሁሉም ወኪል አድርገው እንዲቆጥሩና በአሜሪካ ምክር-ቤትም ሆነ በሌላ መድረኮች ብቸኛ ተወካይ አድርገው እንዲቀበሉ ከፍተኛ ትግል ተደርጓል:: እኔ እራሴ የቅርንጫፉ ፀሐፊ ስለነበርኩ ከሰብሳቢው ከዶ/ር ማንከልክሎት ጋር ተመካክረን ዶ/ር በዬነ የአሜሪካ ኮንግረስ ከሽግግር-መንግሥቱ ጋር ለማደራደር ባዘጋጀው ስብሰባ ላይ ለመገኘት ሲመጡ በሁሉም የተቃዋሚው ስም እንዲሆን በአገር-ውስጥ ያሉ ድርጅቶችን ሙሉ ውክልና ይዘው እንዲመጡ ያ ካልሆነ ግን ምክር-ቤቱን ዋጋ-ቢስ እንደሚያደርገው ቢያንስ ሁለት ጊዜ በስልክ አሳስቤአለሁ:: ሆኖም በመጨረሻ ለመገኘትና ለመሣተፍ የመረጡትና የወሰኑት ሁሉንም ባሰባሰበውና በሚወክለው ምክር-ቤት ሊቀ-መንበርነታቸው ሣይሆን የኢሰዴኃ አንድ አባል ድርጅት በሆነው በደቡብ ኅብረት ስም ብቻ ነው:: ለአንዳዶቻችን ያ እርምጃ ቅስም የሰበረና የምክር-ቤቱን ሁሉን የመወከልና ትግሉን በአንድ አቅጣጫ የማስኬዱ ጉዳይ እንዳከተመለት ያሣዬ ነበር:: በዚኸ ረገድ ተወቃሹ ዶ/ር በዬነ ብቻ ሣይሆኑ ምንም እንኳን የኢሰዴአኃ ቅርንጫፍ-ጽ/ቤት ያልተቋረጠ ትግል ቢያደርግም አንዳንድ ድርጅቶች በምክር ቤቱ ለመወከል ፈቃደኝነት አለማሣየታቸው የምክር-ቤቱ ተቃዋሚውን ወክሎ እንዳይገኝ የሆነው በሁለቱም ወገኖች አርቆ-ያላዬ ውሳኔ ነው ማለት ይቻላል:: ቅርንጫፍ ጽ/ቤቱ የምክር-ቤቱን ሊቀ-መንበርና በውጭ የሚገኙ፣ ያውም የቅርንጫፉ አባል ድርጅቶች መሪዎች ጋር አገናኝቶ የፊት-ለፊት ግልጥ ውይይት እንዲደረግ ያቀደው ዝግጅትም በተለይ በምክር-ቤቱ ሊቀ-መንበር በኩል ከፍተኛ መገርገር ገጥሞት ስለ-ነበር ለችግሩ በቀጣይነት መባባስ አስተዋፅዖ ነበረው::*

***በክፍል አሥራ-ሁለት ይቀጥላል.........***